# “ግማሽ ቀን ከጀግናው ጋር”

# እና

# የምርቃት ቀን !

ይህ ፅሁፍ ለዚህ አመት የጀግና ሜዳይ ተሸላሚዎች ማስታወሻ ትሆን ዘንድ ምኞቴ ነው።

1979 ዓ/ም አጋማሽ ላይ የኦ.ኦ.ሲ 3 የምንባለው የአየር ሃይል ካዴቶች የመመረቂያችን ቀን ነበር።ከኛ በፊት ሁለት የኛ አይነት ምሩቃን ከዚያ ግቢ ወጥተዋል።(ኦ.ኦ.ሲ-1 እና ኦ.ኦ.ሲ-2 ) በአየር ሃይሉ ታሪክ አንድ የነበረው የመኮንኖች ማሰልጠኛ ተቋም መጨረሻ ላይ ሶስት ማድረግ ግዴታ  ሆነ።የመጀመሪያዎቹ ካዴቶች የአየር ሃይሉ አካዳሚ እጩዎች ሲሆኑ ይሄ አካዳሚ ለብዙ ጊዜ ተቋርጦ እንደገና የተጀመረ ነው።የዚህ ተቋም እንደገና መጀመር ላይ የሊቢያው ጋዳፊ እጅ አለበት ይባላል።የመኖሪያ ቤቱን እና የምግብ ቤቱን ያሰሩት እሳቸው ሙኣመር ጋዳፊ ናቸው እየተባለ ይታማ ነበር።እርግጥም ማለፊያ ቤት ነበር።የመዝናኛ ክበቡ ከአውሮፓ ስታንዳርድ እኩል ነበር።ይህ ድሮ ሽብሩ በር ተብሎ ይታወቅ በነበረው ቦታ አካባቢ የተሰራው ድንቅ ቤት እንደገና ከተቋቋመ በኋላ ልዩ የሆኑ የአየር ሃይል ካዴቶችን አስመርቆ አውጥቷል።

ሁለተኛው የአየር ሃይል ካዴቶች ደግሞ እዚያው ግቢ በበታች ማእረግ ሰልጥነው ግልጋሎት ሲሰጡ ከነበሩት ውስጥ ጥሩ ሰራተኞችን፤ደግሞም መልካም ስነምግባር ያላቸውን ያካተተው እዚያው ከአየር ሃይሉ ጦር የሚመመለው ሲሆን፤ሶስተኛው እኛ ነን፤እኛ ደግሞ እኔን ጨምሮ ከራሽያ ሰልጥነን የምንመለሰው ነበርን።ከራሽያ ሰልጥነን የምንመለሰውን እንደገና ወደ አየር  ሃይሉ የምልምል ማሰለጠኛ ገብተን እንድንሰለጥን ሲደረግ የከፋን ብዙ ካዴቶች ነበርን።ራሽያኖቹ ሶስት አመት የተላከንበትን የሙያ ትምህርት ያሰለጥኑን እና መቶ አለቆች ናችሁ ካሁን ወዲያ እንደፍጥርጥራችሁ ብለው ወደ ደብረ ዘይት ይልኩናል። በዚህም ደብረ ዘይት ጎዳና ላይ በየአመቱ እንኳን መኮንን ሆነን አመራር ልንሰጥ እና ሲቪል እንሁ ወታደሮች የማንታወቅ ትንሽ  የአውሮፓ ፀሃይ ያቀላን  ልጆች እንታይ ጀመር።አየር ሃይሉ እንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ እያለ ነው የወቅቱ የአየር ሃይል አዛዥ ጀነራል ፋንታ በላይ አዲስ ዘዴ ይዘው ብቅ ያሉት።

ጀነራሉ አንድ ቀን ስታፎቻቸውን ሰብስበው እነዚህን ልጆች ምን እናድርግ? ብለው የጠየቁ ይመስለኛል።እኚህ በአመራር ብቃታቸው ወደር የማይገኝላቸው መኮንን ለዚያ ጊቢ እንደ አባት ቢሆኑም የራሽያኖቹን እዚያ መኖር በበጎ የሚያዩት አይመስለኝም።ጥሎባቸው ራሽያኖቹን ጠልተዋቸዋል።እኛ ደግሞ የጉዲፈቻ ልጆች አይነት የሆንባቸው ይመስለኛል።ከጊቢው እንዳያባርሩን፤ወሬ እንደነፋስ የሚያመላልሱ ካድሬዎች ፀረ  ኮሚኒስት፤ፀረ ሶቪየት አድርገው ለመንግስቱ እርድ ሊያቀርቧቸው ነው።ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ሁላችንም የዚያች አገር ልጆች ስለሆንን ደግሞም የወታደራዊ ስነስርአቱን ያለማወቅ የኛ ጥፋት ሳይሆን የጊዜው አሰራር የፈጠረው ችግር መሆኑን የተረዱ በመሆናቸው ወደ መፍትሄ ሲሄዱ ለምንስ አንድ አመት ሰራዊቱ ውስጥ ገብተው ሰራዊቱን በሰለጠኑበት ሙያ እያገለገሉ ከሰራዊቱ ጋር አይለማመዱም? ፤ከዚያ በኋላስ የፈለገው ጊዜ ፈጅቶ ልባቸው እስኪጠፋ አሽተን ወታደር አናረጋቸውም ብለው እንደገና ወደ አዲስ ምልምል ትምህርት ቤት ለመከተት አንድ ተቋም ይፈጥራሉ።ተቋሙንም “ኦፊሰርስ ኦሬንቴሽን ኮርስ" ይሉታል።በዚህም ኦ.ኦ.ሲ የሚባል አዲስ የካዴት ትምህርት ቤት ይከፈታል።እኛም ኦ.ኦ.ሶ-3 ተባልን።

ራሽያኖቹ በጀነራሉ ሃሳብ ተናቅን ብለው መንግስቱ ሃይለማርያም ድረስ መሄዳቸውን በሃሜት ደረጃ ኋላ ላይ የሰማን ቢሆንም ሰውየው ግን ጀነራል ፋንታ ናቸው እና “ኔት”(ኖ) በሚል ቀላል የራሽያ ቃል ራሽያኖቹን ዘግተው ሃሳባቸውን ተግባራዊ ያደርጋሉ።“ከዚህ በመቀጠል “ፓቼሙ? “ክቶ ስካዛል”?””!ቾርት የቮ ማቴሪ ! - (ለምን? ማን ነው ይሄን ያለው?፤የሰይጣን ልጅ ሁሉ ) የሚሉ የራሽያ ቃላት ከአፋችን እንደመድፍ  እየተወረወሩ በየሜዳው እየወደቁም ቢሆን የአየር ሃይሉ የትምህርት ምድብ አንድ ክፍል የሆነው የአዲስ ምልምል ትምህርት ቤት ተረከቦን ስራውን ጀመረ።እኔ ወትሮ ለጥቂት ጊዜም ቢሆንም የማውቀው አስር አለቃ ዳርጌ እንደገና እጁ ላይ ወደቅን። ሻምበል ዳዲ፤ሻምበል ተፈራ፤ መቶ አለቃ ተፈራ(ጀበርናው)፤ሌሎችም መኮንኖች ተረከቡን።እርግጥም ጀነራል ፋንታ ልክ ነበሩ ይሄው ከአውሮፓ መልስ በኋላ የራሽያ “ከልባሳ” እና “ቦርሽ” የሚባለው ሾርባ ሆዳችንን የሞላው ጠፍቶ ሁላችንም በረጅሙ የተፃፈ “አንድ ቁጥር” መስለን ለምረቃ አዘጋጁን”።

እኔ በግሌ ዛሬም ድረስ ለማንኛውም ሁኔታ ፈጥኜ መልስ እንድሰጥ እና ማንኛውንም አደጋ  በፀጋ ለመጋፈጥ የሚያስችል ህይወት ለሚባለው ትልቅ  ሂደት ውስጥ ግራ ቀኙን በማየት ውሳኔ ላይ እንድደርስ በአእምሮ እና በጉልበት እንድዘጋጅ እድሉን አገኘሁ።መንግስቱ ናቸው ለምርቃት የሚመጡት የሚሉ ካዴቶች የነበሩ ቢሆንም፤ መንግስቱ ካልሆኑ የመከላከያ ሚኒስትሩ እንደሆኑ ሰምቻለሁ የሚሉ እኛው ጋር አንድ ላይ የምንተኛ እና ሃያ አራት ሰአት  ጎን ለጎን አብረን የምንሄድ ካዴቶችም ሌላ ወሬ ያወሩ  ጀመር።በመጨረሻ ግን የማይቀረው ቀን ደረሰና ትልቁ የአየር ሃይል  ሜዳ ላይ ተሰልፈን የመጨረሻ የሰልፍ ልምምድ ስናደርግ፤“ለጓድ ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ የአየር ሃይል አዛዥ የብረት ሰላምታ ስጥ የሚል ትእዛዝ መጣና በዚሁ የአየር ሃይሉ አዛዥ እንደሚመርቁን አወቅን”።የምረቃው ቀን ጠዋት እንደሌሎች የደብረ ዘይት ጠዋቶች ሁሉ ድምቅ ያለ ቀን ነበር። ለምረቃ እንዲሆን

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በተለምዶ ግራንድ ዩኒፎርም የሚባለውን ልብስ ለበሰን ፤የሚያበራ ሰማያዊ ቀለም ያለው ሸሚዝ ላይ ከግራንድ ዩንፎርሙ ጋር አንድ አይነት የሆነ ከረባት አደረግን።ለካዴት ጢም መላጨት የመጀመሪያ ስራው ቢሆንም ያን ቀን ጉንጫችንን ሁለት ዙር  ሄድንበት።ከረባት እርስ በርሳችን እየተቀባበልን ተሳሰርን፤ይበልጥ  የግራንድ ዩኒፎርሙን ልዩ የሚያደርገውን እና እንደ ባላባት በቅሎ ጌጥ የበዛውን ገመድ በአንድ ጎን በኮታችን ላይ አደረግን፤እስከንመረቅ ድረስ ካዴቶች በመሆናችን ከአየር ሃይሉ የሎጅስቲክ ክፍል የወሰድነውን ሁለት የምክትል መቶ አለቃ ኮከብ ሁላችንም በኪሳችን ያዝን።እኔ በየደቂቃው ያቺን ኮከብ እነካት እንደነበር ዛሬም ድረስ ትዝ ይለኛል።ሰአቱ ሲደርስም ወደ ምረቃው ቦታ ሄድን ።

ወላጅ ዘመድ  አደባባዩን ሞልቶታል፤ታላቅ ወንድሜ አባቴን ወክሎ መጥቷል፤ወንድሜ ከሩቅ እንዳየኝ ሲሮጥ መጥቶ ፎቶ አነሳኝ እና ተመልሶ ወደ ቦታው ሄደ ፤በማርሽ በታጀበ ሙዚቃ እርምጃችን አንድ አድርገን እንቅስቃሴ እናደርጋለን፤አስተማሪ መኮንኖች ልጃቸውን የሚድሩ ይመስል ወዲያ ወዲህ እያሉ አመራር ይሰጣሉ።የፀሃዩ ብርሃን ከበረታ እግራችሁን አንቀሳቅሱ ፤ከመሃላችሁ አንድ ሰው ቢወድቅ ዞር ብሎ ማየት የለም ሰልፉን መቀጠል ብቻ ነው እያሉ ለያንዳንዳችን ማስጠንቀቂያ መሰል ምክርም ይሰጣሉ።

“ሰአቱ ሲደርስ ጀነራል ፋንታ ከስታፎቻቸው ጋር መጡ ።እንደተለማመድነውም የካዴት መሪያችን  እንደዚህ አለ፤ያለማጋነን የሰልፉ መሪ ጩሀት መሃል ገበያው ድረስ ሊሰማ ይችላል፤ በመጀመሪያ ሰልፈኛ !ብሎ ጮሀ ወዲያውም አካባቢው እና የማርሹ ሙዚቃ ዝም ሲል በመቀጠል ተጠንቀቅ ! ካለ በኋላ የራሱን ትንፋሽ ወስዶ ጀነራል ፋንታ በላይ  የክብር ቦታቸውን እንደያዙ ፤ “ለጓድ ሜጀር ጀነራል ፋንታ በላይ የአየር ሃይል አዛዥ በብረት ሰላም በል!” ብሎ አዘዘ። እኛም ድንገት በቃሪያ ጥፊ እንደተመታ ፊት፤ የያዝነውን የክላሽን ኮቭ ጠመንጃ አንድ ላይ ቿ! አድርገን ለአዛዣችን ሰላምታ ሰጠን ።የጠመንጃ አወጣጡ እና አወራረዱ አንድ ላይ ስለሆነ አንድ ሰው ብቻ ያደረገው እስኪመስል ድረስ ብረቱን ጠመንጃ ድንገት ሰማይ ላይ አውጥተን ድንገትም መልሰን በጥፊ አልነው”።ይሄን አድርገንም የያዝነውን ጠመንጃ ማንም እንዳይነጥቀን አድርገን ይዘን በተጠንቀቅ እንደቆምን፤ የረር ጋራው ስር ተደብቀው ይጠብቁ የነበረ የሚመስሉት የአየር ሃይል ጀቶች በሚደንቅ ሁኔታ አራት ሆነው በፓይለቶቹ ቋንቋ “ፎር ሺፕ” ሰርተው በላያችን ላይ አለፉ።አንበሳው ሻለቃ አለማየሁ እሳቱ (BLACKY) ዘወትር እንደዚህ ልዩ በሆነ ቀን እንደሚያደርገው ሚጉን መሬት ለመሬት እየጎተተ አምጥቶ አዋራውን በማጨስ ለበአላችን ልዩ ድምቀት ሰጠልን።በዚህም ፀጥ ብሎ የነበረው የወታደራዊ ማርሽ ጀመረ።

ከብረት ሰላምታው ሰልፍ ቀጥሎ አዛዡ መጠነኛ ንግግር ካደረጉ በኋላ የተመረጡ ካዴቶች ወደ ተዘጋጀው ባንዲራ በመሄድ በቀኝ ጉልበታቸው ተንበርክከው ባንዲራውን ግንባራቸው ላይ አደረጉት። የዚህን ጊዜ ተሰላፊ ካዴቶች ቀድሞ የታደለንን  ትናንሽ ባንዲራ ከኪሳችን አወጣን እናም ድንገት ሁላችንም የራሳችን ስም ጠራን ቀጥለንም “እናት ሃገር ብከዳሽ ውርደት እጣ ፋንታየ ይሁን” ብለን ማልን።(እርግጥም ይሄ መሃላ ዛሬ እየሰራ ይመስለኛል)፤ይሄን ሲሉ ያለቀሱ የነበሩ ጓደኞች ነበሩኝ። የቃለ መሃላው ስነስርአት እንዳበቃ ወደ ጀነራሉ በመሄድ ዲፕሎማ ተቀበልን ። “እንኳን ደስ ያለህ በርታ” የሚል ቃል ተደጋግሞ ከጀነራል ፋንታ አንደበት ይሰማ ጀመር።የዲፕሎማ አሰጣጡ ስነስርአት እንዳበቃ በሰልፍ መሪያችን ትእዛዝ  ወደ ቀኝ አንድ ላይ በመዞር ጥቂት ሄድን እና መጀመሪያ ወደ ግራ  ሄደን ራሳችንን አስተካክለን በአዛዡ  ፊት ለማለፍ ተዘጋጀን።

“የማርሹንም ድምፅ በመከተል ብሬክ ዳንስ በሚመስል ቄንጥ ወደ አዛዡ እና ወደ ተሰበሰበው ሰው አመራን።ጀነራሉ ፊት ለፊት እንደደረስንም መሪያችን ሻሞላውን ሰማዩን ቀዶ እስኪወጣ ድረስ ሰቅሎት እንደገናም እየጮሀ፤ እንደገናም የሻሞላውን ዘንግ እያንቀሳቀሰ እና ከፀሃይዋ ብርሀን ጥቅስ እያደረገ፤ ድጋሚ ስማችንን ጠርቶ ሰልፈኛ! አለና ራስ ቀኝ ብሎ ሻሞላውን ከብርሃን እና ከድምፅ በፈጠነ ሁኔታ ከሰቀለበት ሰማይ አውርዶ ወደ መሬት ላከው። በርግጥም የዚህን ጊዜ ሰልፈኞች ሁሉ ራሳችንን ቀጥ አድርገን ታዛዥነታችን በሚገልፅ ሁኔታ እጃችንን አስረን ዞር ብለንም በትከሻችን ትክክል ወደ ጀነራል ፋንታ እና  አጠገባቸው ወዳሉት የአየር ሃይሉ ቺፍ ኦፍ ስታፍ ወደ ጀነራል አምሃ ደስታ እያየን ሰላምታ መስጠት ጀመርን።እንደተለማመድነውም፤ አስር አለቃ ዳርጌ እንዳሰለጠነንም፤ከሰላምታው በኋላ ሰባት ግራ እግር ቆጥረን ለሰላምታ አጥፈን የነበረውን አንገታችንን መለስን። በየመቶው ያለው ሰልፈኛም በዚሁ አይነት አለፈ። የምረቃ በአሉም ማለቂያ ሆነ”።

ያቺ ድሃ አገርም፤ያቺ የአፍሪካ የነፃነት ተምሳሌት አገርም ፤ያቺ የጀግኖች አገርም ፤የነ በላይ ዘለቀ፤የነ አብዲሳ አጋ፤ የነ ኡመር ሰመተር፤ የነ አማን አምዶም፤ የነ ለገሰ ተፈራ፤ የነ አሊ በርኬ፤የነ ጀነራል ተስፋየ ሃብተማርያም፤ደግሞም የጀነራል ካሳየ ጨመዳ አገር (እኔ እማማ ኢትዮጵያ የምላት) ድንቅ የሆኑ ከእሳቱ ላይ እንደወረደ ጀበና የሚሞቁም አዲስ ትኩስ መቶ አለቆች አገኘች። እኔም አንዱ ነበርኩ።በጊዜው ለኩራቴ መጠን ልክ አልነበረኝም።ሁሉም ነገር አልፎ ዛሬ ያለንበት ደረጃ መደርሳችን ዘወትር እንደ ክፉ ህልም ማሰቡ ቢያስጠላኝም አንድ ወቅት በደብረ ዘይት ሰማይ ላይ  እንደዚህም ሆኖ አልፏል።

**ወሰኔ**...

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com